የሰ/መ/ቁ. 44522

ታህሣሥ 15 ቀን 2003

**ዳኞች**:- ተሻገር ገብረሥላሴ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**:- ጭላሎ ሥራ ተቋራጭ የተወሰነ የግል ማህበር አልቀረበም

**ተጠሪ**:- አፍሪካ ኢንጅነርስ ኮንስትራክሽን ጠበቃ አቶ ተሰማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የማሽነሪ ኪራይ ውል አፈፃፀምን የተመለከተ ነው ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ከሣሽ በመሆን አንድ ግሬደር በሰዓት ሁለት መቶ ሃምሣ ብር ላንድሮለር በሰዓት ሁለት መቶ ብር አንድ ዶዘር በሰዓት አራት መቶ ብር ሊከፍል የአሁን አመልካች /ተከሣሽ/ የወሰደ መሆኑን ገልፆ ያልተከፈለ የማሽነሪ ኪራይ ብር 1,327,500.00/አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃያ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብር/ ያለበት ስለሆነ እንዲከፍለኝና ማሽነሪዎቹን እንዲያስረክበኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ /ተጠሪ/ የጠየቀው ማሽነሪዎቹ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በዝናብና በጎማ አለመኖር ለቆሙበት ሰዓት በመሆኑና የሠሩበት ሠዓት በሹፌሮቹ ተረጋግጦ የቀረበ ባለመሆኑ ክሱ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሣሽ /ተጠሪ/ ያቀረበውን ክስ የሚያስረዳ ማስረጃ ያቀረበ በመሆኑና አመልካች /ተከሣሽ/ የኪራይ ገንዘብ ትክክል አይደለም በማለት ከሚከራከር በስተቀር ክርክሩን የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሒሣቡ በባለሙያ ተጣርቶ መቅረብ እንዳለበት በማመን አመልካች አንድ ባለሙያ ተጠሪ አንድ ባለሙያ እንዲመርጡና ሒሣቡን ሁለቱ ባለሙያዎች በጋራ አጣርተው እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሁለቱ ባለሙያዎች በጋራ ሒሣብ እንዲያጣሩ የተሰጡትን ትእዛዝ ወደ ጎን በመተው አመልካች የመረጠው ባለሙያ ሒሣቡን ለብቻው በማጣራት አመልካች ለተጠሪ ያልከፈለው ብር 54,267.17 /ሀምሣ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሥልሣ ብር ከአሥራ ሰባት ሣንቲም/ ነው በማለት የሒሣብ ሪፖርት ለብቻው ያቀረበ ሲሆን በተጠሪ

የተመረጡት ባለሙያ በበኩላቸው አመልካች በተጠሪ ያልከፈለው ቀሪ ሒሣብ ብር 1,327,005 /አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሃያ ሰባት ሺህ አምስት ብር/ አለበት በማለት የብቻውን የሒሣብ ሪፖርት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካች የተመረጠው ባለሙያ ያቀረበው ጥቅል የሒሣብ ሪፖርት መሆኑና በተጠሪ በኩል የተመረጡት ባለሙያ ዝርዝር የሒሣብ ሪፖርት ያቀረቡ መሆኑን በመግለጽ በተጠሪ የተመረጠው ባለሙያ ያቀረበው የሒባብ ሪፖርት አሣማኝነት አለው በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት አመልካች ለተጠሪ ብር 1,327,005 እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የኪራይ ሒሣቡ በባለሙያ ሣይጣራ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሰጠቱ በአግባቡ መሆኑን በማመን ሒሣቡ በባለሙያ እንዲጣራ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በባለሙያዎቹ ሒሣቡን በጋራ በማጣራት የሚስማሙባቸውን ሒሣብ ተስማምተው የተለያዩበትን ሒሣብ የልዩነታቸውን ምክንያት በመግለጽ በጋራ ማቅረብ ሲገባቸው ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከሰጠው ትእዛዝ ውጭ ለየብቻ ሠርተው ካቀረቡት ሪፖርት ውስጥ የአንደኛውን ባለሙያ ሪፖርት በመተው ሌላውን ተቀብሎ የሰጠው ውሣኔ ስለ ልዩ አዋቂ ምስክር የተደነገገውን የማያሟላና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በቃል ክርክር ባቀረቡት መልስ ችሎት ሒሣቡን በዝርዝርና በሚያሣምን ሁኔታ ሠርቶ ያቀረበለትን ባለሙያ በመቀበል ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በጋራ ሒሣቡን እንዲያጣሩና ሪፖርት እንዲያቀርቡለት ትእዛዝ የሰጣቸው ባለሙያዎች ለየብቻ ሒሣብ በማጣራት ያቀረቡትን ሪፖርት በመቀበል የአንደኛውን ባለሙያ የሒሣብ መግለጫ ውድቅ በማድረግና የሌላውን ትክክለኛ ነው በማለት ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ እልባት ለመስጠት በአገራችን የሕግ ሥርዓት ልዩ አዋቂ ምስክር በፍርድ ቤቱ የሚሾምበትን ምክንያት በዝርዝር ማየት ያስፈልጋል፡፡ የኮመንሎው የሕግ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች ተከራካሪዎች ልዩ አዋቂ ምስክሮቻቸውን በራሣቸው የማቅረብና በተከራካሪዎች ምርጫና ክፍያ የማይቀርበው ልዩ አዋቂ ምስክር የቀጠራቸውን ተከራካሪ ሊረታ የሚችልበትን ሁኔታ ከሙያ አንፃር አቀነባብረው የሚያቀርቡ የሲቪል ሎው በሚከተሉ አገሮች የልዩ አዋቂ ምስክር የሚመድበው በፍርድ ቤት ሲሆን የልዩ አዋቂ ምስክሩ በማናቸውም ተከራካሪ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ከሙያ አንፃር ማጣራት የሚገባውን ነገር አጣርቶ ለፍርድ ቤቱ የሚያቀርብና የሙያ አበልም የሚታሰብለት በፍርድ ቤቱ በኩል እንደሆነ የሕግ ሥርዓቱን የሚከተሉ የሥነ ሥርዓት ሕግጋት በማየት ለመረዳት ይችላል፡፡

የአገራችን የሕግ ሥርዓት የሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓት የሚከተሉ አገሮች የሚከተሉትን መሠረታዊ መርህ የሚያራምድ ሲሆን አከራካሪ ጉዳይ የሚያጣሩ ልዩ አዋቂዎች /ባለሙያዎች/ ጉዳዩን አጣርተው እንዲቀርቡ የሚሾመው ፍርድ ቤቱ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 ተደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሚሾማቸው ልዩ አዋቂ ምስክሮች ከተከራካሪዎቹ አንደኛውን ለመደገፍ ሣይሆን ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ትእዛዝ የሙያ ሥነ ምግባር የሚጥልባቸውን ግዴታ ተከትለው ገለልተኛ ሆነው ፍሬ ጉዳዩን በመመርመር ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

አለባቸው፡፡ በፍርድ ቤቱ የተመደቡ ልዩ አዋቂ ምስክሮች የሙያ ምግባር የሚጥስ ወይም ገለልተኛ በመሆን ከሙያ አንፃር ጉዳዩን መርምረው ማቅረባቸው አከራካሪ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በሌላ ባለሙያ እንዲጣራ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ባለሙያዎቹን ሲመድብ ነፃና ገለልተኛ የሆኑ ባለሙያዎች በመምረጥ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136/1/ መሠረት ባላቸው ልዩ የሒሣብ እውቀት ሒሣቡን መርምረው መመደብ ሲገባው አመልካች የራሱን ባለሙያ እንንዲያቀርቡ ማድረጉ ተገቢነት አልነበረውም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ባለሙያዎቹ በጋራ ሒሣቡን ሠርተው እንዲያቀርቡ የሰጣቸውን ትእዛዝ ባለሙያዎቹ አላከበሩም፡፡ ባለሙያዎቹ የፍርድ ቤቱ ልዩ አዋቂ ምስክር ሆነው ከተሰሙ በኋላ ከሁሉም በላይ ለፍርድ ቤቱ ትእዛዝና መመሪያ ተገዥ በመሆን የሙያ ሥራቸውን ማከናወን አለባቸው የልዩ አዋቂ ሒሣብ አጣሪዎች የችሎቱ ትእዛዝና በመመሪያ መጣስ አመልካች የመደበው ባለሙያ የአመልካችን ክርክር በመደገፍ የሒሣብ ሪፖርት ተጠሪ የመረጠው ባሉሙያ ተጠሪን በመደገፍ የሒሣብ ሪፖርት አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሁለቱም ምስክሮች ችሎቱ ከሰጣቸው ትእዛዝና መመሪያ ውጭ ሒሣቡን በተናጠል ሠርተው ሲያቀርቡለት የሁለቱንም ሪፖርት ውድቅ በማድረግ ሂሣቡ በሌላ ባለሙያ ወይም ኦዲት ለማድረግ በተቋቋሙ ሕጋዊ ድርጅት በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠት ነበረበት፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጣቸው ትእዛዝና መመሪያ ተመርተው ሒሣቡን ያላጣሩ መሆኑን እያወቀና ችሎቱ ከሰጣቸው ትእዛዝ ውጭ ሁለቱም ባለሙያዎች በተናጠል የመሰላቸውን ሁለት የሂሣብ መግለጫ ካቀረቡለት በኋላ በአመልካች በኩል የተመረጠው ባለሙያ የቀረበው ጥቅል ሒሣብ ስለሆነ አሣማኝ አይደለም ከተጠሪ የተመረጠው ባለሙያ ያቀረበው ዝርዝር ሪፖርት ስለሆነ አሣማኝ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ስለ ልዩ አዋቂ አጣሪ አመዳደብና አሠራርና የተዘረጋውን ሥርዓትና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 ድንጋጌን የሚቃረን በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ብቃት ያለው ገለልተኛ የሒሣብ ባለሙያ ወይም ፈቃድ ያለው የኦዲት ድርጅት በመመደብ ሒሣቡ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ